# ቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶችና ትርጉማቸው

| | | |
|---|---|---|
|  ድ ፋ ት | ድፋት | ድፋት በቅርጹ ስንመለከተው ጎንበስ ብሎ ወደታች የሚመለከት ነገር ይመስላል ትርጓሜውም ጌታችን ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከቅድስት ድንግል ማርያም ተወልዶ ሰው መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡አጠቃቀሙም ድምጽን አንገትን ወደ ታች እርግጥ አድርጎ ወይም ደፍቶ ትንፋሽን ወደ ሆድ ውስጥ በመመለስ ማዜም ማለት ነው |
|  ሂደት | ሂደት | ሂደት በቅርጹ ስንመለከተው ረዘም ያለና ወደጎን የተሰመረ መስመር ሆኖ በስተግራ በኩል በላዩ ላይ ጀልባ መሰል ቅርጽ ያለው ሆኖ እናገኘዋለን ይህም የሚያሳየው መሄድን፤መጓዝን፤መራመድን ነው፡፡ ትርጓሜውም ጌታችን በዚህ ዓለም ከቦታ ቦታ እየተዘዋወረና በባሕር በየብሱ እየተመላለሰ ማስተማሩን እንዲሁም አይሁድ አንድ ጊዜ ወደ ቀያፋ አንድ ጊዜ ወደ ሄሮድስ እየወሰዱ እንዲንገላታ ማድረጋቸውን የሚያስረዳ ነው፡፡አጠቃቀሙም እንደ ሜዳ መንገድ፤እንደ ቦይ ውኃ ወይም ሰተት ብሎ እንደሚሔድ ተጓዥ አንተም ሳታቆም(ሳታቋርጥ) ምንም ነገር ሳትይዝ ሰተት ብለህ አዚም ማለት ነው፡፡ |
|  ቅናት | ቅናት | ቅናት በቅርጹ ቀጥ ያለና ከቀኝ ወደግራ የተሰመረ ወልጋዳ መስመር ይመስላል ይህም ቅን ያልሆነን ጠማማ ነገር የሚያመለክት ነው፡፡ ትርጓሜውም ጌታችን በአምላክነቱ በሽተኞችን መፈወሱ ሙታንን ማስነሳቱ ያስቀናቸው ካህናተ አይሁድ ጠማማ በሆነ አእምሮአቸው ተመቅኝተው እንዲሰቀል ማድረጋቸውን የሚያሳይ ነው፡፡አጠቃቀሙም በዜማው ቃል መጨረሻ ያለውን አንዱን የፊደል ሆሄ ይዘህ አንገትን ወደ ላይ በማቅናትና ድምጽን እንቅ በማድረግ አዚም ማለት ነው፡፡ |
|  ይዘት | ይዘት | ይዘት በቅርጹ ተጨማሪ የሌለው አንድ ነጥብ ነው ይህም ተጨማሪ ነገር የሌለው አንድ ብቻ የሆነን ነገር የሚያመለክት ነው፡፡ ትርጓሜውም ከጽድቅ በቀር ሌላ ኃጢአትና በደል(ጥፋት) የሌለበትን አኃዜ ዓለም የሆነውን ጌታችንን አይሁድ ይዘው ለሞት መዳረጋቸውን የሚገልጽ ነው፡፡አጠቃቀሙም በዜማ አጠቃቀም ጊዜ በፍጥነት ከሚዜመው ዘር አንዱን የፊደል ሆሄ ያዝ በማድረግ አዚም ማለት ነው |
|  ቁርጥ | ቁርጥ | ቁርጥ በቅርጹ ከላይ ወደታች ቀጥ ያለመስመር ሆኖ በቀኝ ጎኑ በኩል ትንሽ ተቀጥላ ያለው ነው ቅርጹ በአጠቃላይ የመጥረቢያ ዓይነት ቅርጽ አለው ይህም አንድን ነገር ለመቁረጥ የተዘጋጀ መሣሪያን ያመለክታል፡፡ ጌታችንም ራሱን ለመከራ አሳልፎ በመስጠት ነፍሱን ከስጋው ለመለየት ቁርጥ ውሳኔ ማድረጉን ያመለክታል፡፡አጠቃቀሙም ዜማውን በምታዜምበት ጊዜ ድምጽን በመጠኑ በመቀነስ፤ትንፋሽን ወደታች በማመቀን እንደገናም ድምጽን በማጋነንና አገጭን ወደ ፊት ገፋ በማድረግ አዚም ማለት ነው |

# ቅዱስ ያሬድ የዜማ ምልክቶችና ትርጉማቸው

| | | |
|---|---|---|
|  ጭረት | ጭረት | ጭረት በቅርጹ የተጣመመና ጎባጣ መሰል ነገር ሆኖ ይታያል ይኸም ራሰ ጎባጣ ወይም ራሰ ጠማማ የሆነ በትርን ያመለክታል ትርጓሜውም ጌታችን በበትር መመታቱን ያመለክታል አጠቃቀሙም በዘር መካከል ያለውን አንዱ የፊደል ሆሄ ወደ ጎን ጨር በማድረግ አዚም ማለት ነው |
|  ርክርክ | ርክርክ | ርክርክ በቅርጹ ሲታይ የሚንጠባጠቡ ነገሮች ይመስላል ትርጓሜውም ጌታችን ሲገረፍና ሲሰቀል ከሰውነቱ የተንጠባጠበውን የደምና የላብ ነጠብጣብ የሚያመለክት ነው። አጠቃቀሙም ረጅም የሆነውን ዜማ በላዩ ላይ ርክርክን በመጨመር በረጅሙ አዚም ማለት ነው። |
|  ደረት | ደረት | ደረት በቅርጹ ሲታይ ከታች ወደላይ የሚመለከት ነገር ይህም አንድ ተኝቶ የነበረን ሰው አፈፍ ብሎ ሲነሳ የሚያሳይ ቅርጽ ነው። ትርጓሜውም ጌታችን ተሰቅሎ ከሞተና ከተቀበረ በኋላ ሞትን ድል አድርጎ በራሱ ሥልጣን ከመቃብር አፈፍ ብሎ በመነሳት ወደ ሰማየሰማያት ማረጉን ወይም መውጣቱን የሚያስረዳ ነው። አጠቃቀሙም ደረትን ከፍ በማድረግና አንዱን የፊደል ሆሄ ወደ ላይ ቆንጠጥ በማድረግ ማዜም ማለት ነው |

## ከቅዱስ ያሬድ በኋላ የተነሱ ሊቃውንት የጨመሯቸው ምልክቶች

| | | |
|---|---|---|
|  ድርስ | ድርስ | ድርስ በቅርጹ ሲታይ ራሱን ወደ ሰማይ ቀና አድርጎና በሁለት እግሩ በአስተማማኝ ሁኔታ ቀጥ ብሎ የቆመን ሰው ይመስላል ይህም የተነገረው ትንቢት የተቆጠረው ሱባዔ አንድም ሳይቀር መፈጸሙን የሚያመለክት ነው አጠቃቀሙም የቃል መጨረሻ የሆነውን አንዱን የፊደል ሆሄ ያዝ በማድረግና ድምጽን ወደ ኋላ በመሳብ ዜማውን እስከ መድረሻው ማዜም ማለት ነው። |
|  አንብር | አንብር | በቅርጹ ሲታይ ወደ ላይ ወደታችና ወደ ግራ ያለው መስመር የገጠመ ሆኖ ወደ ቀኝ ያው ብቻ ክፍት የሆነ ቅርጽ ነው ይኸም ሁለት ምስጢራት የሚገልጽ ነው<br>1. ጌታ የማዳን ስራውን ሁሉ ጨርሶ በአባቱ ቀኝ መቀመጡን<br>2. ሰዎች በግራ የተመሰለ ግብረ ኃጢአትን ትተው በቀኝ የተመሰለውን ግብረ ጽድቅ ብቻ በመስራት ቢኖሩ በዕለተ ምጽአት በቀኝ በኩል እንደሚቀመጡ ያመለክታል አጠቃቀሙም የአንዱን ዘር መጨረሻ ሆሄ ያለምንም ተጨማሪ ድምጽና ርክርክ በማስቀመጥ /በማቆም አዚም ማለት ነው። |